# የ2ኛ ክፍል የውጤት መስጫ ክፍለጊዜ 1 የወላጆች መመሪያ

በውጤት መስጫ ክፍለጊዜ 1፣ የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ቀጥሎ በተገለጹት ፅንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ተምረዋል።

እባክዎ ልብ ይበሉ፦ በ ግራጫ/አመድማ ቀለም የእውቀት እና ፅንሰሃሳብ ትምህርት ተሰጥቷል ነገር ግን በሪፖርት ካርድ ላይ ማርክ አልተጻፈም።

## የሒሳብ ትምህርት

### ቁጥሮችና ግብረቶች በአስሮሽ ቤት

- የ 3-አሃዝ ቁጥር የሚወክለው መጠን መቶ ቤት፣ አስርዮሽ ቤት እና የአንድ ቤት መሆኑን ተረዳ/ተረጂ።
- በ1000 ውስጥ መቁጠር፤ በ5ቶች፣ በ10ሮች፣ እና በ100 እየዘለሉ መቁጠር።
- አስርዮሽ ቤት አሃዞችን፣ የአሃዝ ስሞችን፣ እና በትንታኔ/የተስፋፋ ፎርም በመጠቀም እስከ 1000 ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ። (ለምሳሌ፦ 512 የሚለው ቁጥር 512 ተብሎ ሊጻፍ ይችላል ወይም 500+10+2 ተብሎ ይጻፋል)።
- >, =, እና < በመጠቀም ባለ 3 - አሃዝ ቁጥሮችን አወዳድር/ሪ።
- በ 100 እና 900 መካከል ካሉት ቁጥሮች ውስጥ 10 ወይም 100 ን በተሰጠ ቁጥር ላይ  በአእምሮ መደመር ወይም መቀነስ።

### ስሌቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- ከ10 ያነሱ ቁጥሮችን በአእምሮ መደመር እና መቀነስ።
- እንደ .. የመሳሰሉትን ስልቶችን በመጠቀም እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ደምር(ሪ) ቀንስ(ሺ)
  - o በመቁጠር፤
  - o በዚህ መልክ አስር በማድረግ(ምሳሌ፣ 8 + 6 = 8 + 2 + 4 = 10 + 4 = 14)፤
  - o ወደ ኣስር የሚመራ ቁጥርን መበተን (ለምሳሌ፦ 13 - 4 = 13 - 3 - 1 = 10 - 1 = 9)፤
  - o በመደመር እና በመቀነስ መካከል ባለው ግንኙነት በመጠቀም (ለምሳሌ፣ 8+4= 12 እንደሚሆን በማወቅ፣ 12-8= 4) እንደሚሆንም ይታወቃል፤
  - o ተመጣጣኝ ነገር ግን ቀላል ወይም የሚታወቅ ድምር መፍጠር (ለምሳሌ፦ 6 + 7 በመደመር የሚታወቀውን ተመጣጣኝ መፍጠር 6 + 6 + 1 = 12 + 1 = 13)።
- ከ20 በታች ያሉ ቁጥሮችን በመደመር እና በመቀነስ በቃላት የተጻፉ ፕሮብሌሞችን በሁሉም ቦታ ላይ ያልታወቁ ቁጥሮችን በማስገባት/በመተካት ማቃለል/መፍታት።

### አለካከና መረጃ

- እስከ አራት ረድፍ መረጃ የሚይዝ ስዕላዊ ግራፍ እና የቁም ግራፍ መሳል።
- በስዕላዊ ግራፍ ወይም በቁም ግራፍ ላይ የተጻፈውን መረጃ በመጠቀም ፕሮብሌም ማቃለል/መስራት።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፦ ስነ ፅሁፍ

- ማን፣ ምን፣ ዬት፣ መቼ፣ ለምን፣ እና እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅና በመመለስ በፅሁፍ/ምንባብ ላይ ያሉ ቁልፍ ዝርዝር መረዳትን ማረጋገጥ።
- በአንድ ትረካ ላይ ያለ ገፀ-ባህርይ አንድን ዋና ሁነት/ዝግጅት እና አስቸጋሪ ሁኔታን እንዴት እንደተቋቋመ ማስረዳት።
- የኣንድ ታሪክን ኣጠቃላይ መዋቅር መግለፅ፣ መጀመርያው ታሪኩን እንዴት እንደሚያስተዋውቅ እና መጨረሻውም ተግባሩን እንዴት እንደሚያጠቃልለው በማካተት።
- በገጸባሕርያት መካከል የኣስተያየቶች ልዩነቶችን ማወቅ፣ በከፍተኛ ድምፅ ንግግርን ሲያነቡ ለያንዳንዱ ገፀባህርይ በተለየ ድምፅ መናገርን ጨምሮ።
- ከተለያዩ ደራሲዎች ወይም ከተለያዩ ባህሎች የተደረሱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የተለያዩ የአንድ ታሪክ ትርጉሞች (ለምሳሌ፣ የሲንደሬላ ታሪኮች) ያነጻፅሩ እና ያወዳድሩ።
- በሁለተኛ ክፍል ደረጃ በአግባቡ ውስብስብ የሆነ ስነ-ጽሑፍን አንብቦ በትክክል የመረዳት ችሎታ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፦ መረጃዊ

- ማን፣ ምን፣ ዬት፣ መቼ፣ ለምን፣ እና እንዴት ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መልስ በመስጠት የጽሑፍን ዝርዝር ሃሳብ መረዳት ችሎታ ማሳየት።
- የ2ኛ ክፍል ደረጃን በሚመጥን ጽሑፍ ርእስ ወይም ትምህርት ላይ የቃላት እና ሐረጎች ትርጉም መወሰን።
- የተለያዩ የጽሑፍ ገጽታዎችን በመጠቀም(ለምሳሌ፦ የምስል መግለጫ፣ ጉልህ ጽሁፍ፣ ንኡስ ርእሶችን፣ የቃላት መፍቻ፣ ኤሌክትሮኒክ ምልክቶችና፣ ተምሳሌት ምልክቶችን) ዋነኞቹን እውነታዎች በፅሁፍ ውስጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ማግኘት።
- ደራሲው/ዋ ምን መልስ መስጠት፣ ማብራራት፣ ወይም መግለጽ እንደሚ(ምት)ፈልግ በመጨመር፣የጽሑፉን ዋና ዓላማ መግለጽ።
- የተለዩ ምስሎች (ለምሳሌ፦ ማሽን እንዴት እንደሚሰራ የሚያሳይ ንድፍ )እንዴት ለጽሑፍ/ምንባብ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ እና እንደሚገልጽ ማስረዳት/ማብራራት።
- በጽሑፍ ላይ ደራሲ የተለዩ ነጥቦችን ለመደገፍ ምክንያቶችን እንዴት እንደተጠቀመ(ች)ባቸው በመዘርዘር ግለጽ/ጪ።
- ለ2ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆኑ መረጃያዊ ፅሁፎችን ማንበብ እና መገንዘብ።

### ቋንቋ፦ የቃላት ዝርዝር ግኘት እና አጠቃቀም

- ስለ ሁለተኛ ክፍል ርእሶች እና ፅሁፎች በኣነስተኛና በትላልቅ ቡድኖች ውስጥ ከእኩዮችና ኣዋቂዎች ጋር ከተለያዩ ሽርኮች ጋር በሚካሄዱ የትብብሮች ዉይይት ውስጥ መሳተፍ።
- ከጽሑፍ ከፍ ባለ ድምጽ ከተነበበ ምንባብ፣ ወይም በቃል የተነገረ ወይም ከሌላ ሚድያ ቁልፍ ሃሳቦችን በመውሰድ በዝርዝር መናገር/ማስረዳት።
- በአንድ ተናጋሪ የተነገረ ሃሳብን በተናጋሪው/ዋ  በኩል ምን እንደተባለ መረዳትን ለመግለጽ፣ ተጨማሪ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ወይም ስለ ርዕሱ ወይም ጉዳዩ በጥልቀት ለመረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መመለስ።
- ያልታወቁ ወይም በርካታ ትርጉም ያላቸውን ቃላት እና ዓረፍተነገሮች ለ2ኛ ክፍል ምንባብ ይዘት ከተደረደሩት ስልቶችን በመለዋወጥና በመምረጥ ትርጉማቸውን መግለጽ።

### መሰረታዊ ክህሎቶች

- መደበኛ የክፍለ ቃል/syllable ቃላት እያነበብክ/ሽ አጫጭር እና ረዣዥም አናባቢዎችን ለይ።
- ለተጨማሪ የወል አናባቢዎ ቡድኖች የሚገጥሙ ፊደላትን-ድምፅ መስተጋብሮችን እወቅ/ቂ።
- በክፍል-ደረጃ ተገቢ የሆኑ ያልተለመዱ የተጻፉ ቃላትን ይገንዘቡ እና ያንብቡ።
- ቃላትን በመነሻ እና በመድረሻ የወል ቅጥያ ምልክቶች ተርጉም/ሚ።

## ጽሑፍ

### ትረካ

- በጣም የተራቀቁ ክስተቶችን ወይም አጭር ተከታታይ ክስተቶችን የሚያወሱ ትረካዎችን ይጻፉ።
- ድርጊቶች፣ ሃሳቦች፣ እና ስሜትን ዝርዝር ሁኔታ ለማብራራት ጊዜያዊ/ወቅታዊ ቃሎችን በመጠቀም የድርጊቶቹን ዝርዝር ሁኔታ ቅደምተከተል በምልክት ማሳየት።
- የመዝጊያ መልእክት መስጠት።

### ትምህርት ሰጭ/ገላጭ

- አንድ ርዕሰ ጉዳይ ማስተዋወቅ እና ነጥቦችን ለማንፀባረቅ ሀሳቦችን እና መግለጫዎችን የሚጠቀሙበት ትምህርታዊ/የሚያብራራ ጽሑፍ ይፃፉ።
- የመደምደሚያውን ሃሳብ ወይም ክፍል ያቅርቡ።

### ኣስተያየት

- ስለሚያስተዋውቁት ርእስ ወይም የሚጽፉትን መጽሐፍ ሃሳቡ ስለምን እንደሆነ ገልጾ መጻፍ።
- የእነርሱን ሃሳብ የሚደግፉ ምክንያቶችን ያቅርቡ።
- አገናኝ ቃሎችን በመጠቀም (ለምሳሌ፦ ስለዚህ፣ ደግሞ/በተጨማሪ፣ እና/እንደዚሁም) ሃሳብ እና ምክንያቶችን ማዛመድ እና የመደምደሚያ ሃሳብ ወይም ክፍል መስጠት።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- በአዋቂ/ትልልቅ ሰዎች እና እኩያሞች ጋር በመመራትና በመታገዝ በርዕሱ ላይ በማተኮር ክለሳ በማድረግ ኃሳብ መቃኘት እና እንደ አስፈላጊነቱ መጻፍን ማጠናከር።
- ከእኩዮች ጋር መተባበርን ጨምሮ፣ ልዩ ልዩ አሃዛዊ ምስል መግብሮችን (digital tools) በመጠቀም የሕትመት ጽሑፍ ማዘጋጀት።
- በጋራ የሚከናወኑ የጥናትና ጽሑፍ ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍ (ለምሳሌ፦ በአንድ ርእስ የተለያዩ መጽሐፍት ማንበብ እና ሪፖርት ማቅረብ፤ የሳይንስ ምልከታዎችን መዘገብ) እና መረጃዎችን ከተሞክሮዎች ማስታወስ ወይም ጥያቄ ለመመለስ ከቀረቡ/ከተሰጡ ምንጮች መረጃዎችን ማሰባሰብ።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- የተፈጸመ ታሪክ  የተረጋገጠ/ሐቅ ላይ በመሞርኮዝ በተቀናበረ ሁኔታ ገላጭ እና ዝርዝር ቃላትን በመጠቀም የተቀናጀ አረፍተነገር ማስደመጥ።
- ቅጽል እና ተወሳከግስ በመጠቀም ገላጭነታቸው ስም ወይም ግስ ከሆነ ከሁለቱ መምረጥ።
- ሃሳብን በማፍለቅ፣ በማስፋት፣ እና በማስተካከል የተሟላ የነጠላ እና ድርብርብ አረፍተነገሮች መስራት (ለምሳሌ፡- ልጁ ፊልም ተመለከተ፣ ትንሹ ልጅ ፊልም ተመለከተ፣ የድርጊቱ ፊልም በትንሹ ልጅ ታይቷል)።
- በመደበኛ የእንግሊዝኛ ትልቁን ፊደል መጠቀም፣ ስርአተ ነጥብ አገባብ/አጠቃቀም፣ እና የቃላት አፃፃፍ ችሎታ/ብቃት አሳይ።
- በአፃፃፍ፣ ኣነጋገር፣ በምንባብ፣ ወይም በማዳመጥ በቋንቋ እውቀት እና በህጎቹ መጠቀም።

## ሳይንስ

### ፊዚካል ሳይንስ

- በሚታዩት ይዘቶቻቸው የተለያዩ ዓይነት ቁሳቁሶችን ለመግለፅ እና ለማጣራት ምርመራ ማቀድ እና ማካሄድ።
- አንዳንድ በሙቀት ወይም በቅዝቃዜ ምክንያት የተከሰቱ ለውጦች ወደነበሩበት ሊመለሱ እንደሚችሉ እና ጥቂቶቹን ወደነበሩበት ቅርጽ/ይዘት እንደማይመለሱ በማስረጃ የመከራከሪያ ሃሳብ አቅርብ/ቢ።
- አንድ ከትናንሽ ነገሮች የተሠራ አነስተኛ ቁስ አካል እንዴት ሊነጣጠል እና አዲስ ቁስ አካል ሆኖ ሊሠራ እንደሚቻል በማስተዋል በመረጃ-የተደገፈ ሪፖርት ለማዘጋጀት ጥናት አድርግ/ጊ።

### ምህንድስና ንድፍ እና ሂደት

- አንድን ችግር ለመፍታት የአንድ ቁሳዊ ነገር በሚፈለገው አይነት መሥራት እንዲችል ቅርጽ እንዴት እንደሚረዳ ለማስረዳት ቀላል ንድፍ፣ ስዕል፣ ወይም አካላዊ ሞዴል አዘጋጅ/ጂ።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ስነ-ዜግነት

- ደንቦች እና ህጎች እንዴት እንደሚፈጠሩ እና ዜጎችን ለመጠበቅ ሥርዓት አስፈላጊ መሆኑን አስረዳ/ጂ።
- የዲሞክራሲ ክህሎቶች እና አመለካከቶች ሃላፊነት/ተጠያቂነት ከሚሰማው ዜጋ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ማስረዳት።
- በት/ቤት እና በማህበረሰብ ተሳታፊ ለመሆን መብት እና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን መግለጽ።

### ባህል

- ሰዎች የሚገናኙባቸውን መንገዶች መተንተን።

## የመረጃ/የኢንፎርሜሽን መሠረተ ትምህርት

- መረጃ መለዋወጥ አስፈላጊነቱን በተለያየ ዓይነት ቅርፀት በመጠቀም የግኝት ውጤት እና ድምዳሜ ማዘጋጀት።
- የተሰጠ/የተመደበ ወይም በግል የሚያስፈልግ መረጃ መለየት።
- ለፍጆታ ስለሚያስፈልግ የተቀረፀ/የተመዘገበ ውሂብ/መረጃ ጥራት መገምገም እና መተንተን።
- ልበወለድ እና ልበወለድ ያልሆነ ስነጽሑፍ ከእውነታ ጋር ያለውን ግንኙነት መለየት።
- መረጃ ለማግኘት የተለየ ምንጭ መጠቀም።
- ውሂብ/መረጃ በተለያየ ቅርፀት መቅረፅ/መመዝገብ።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።

## ስነጥበብ

### ስነጥበብ አቀራረብና ዝንባሌ/ምላሽ

- በአካባቢ እና በሚታዩ ዕቃዎች ዉስጥ ቀለሞችን፣ መስመሮችን፣ ቅርፆችን፣ አወቃቀር/ሥሪት፣ ቅፆችን፣ እና ባዶ ቦታ መግለፅ።
- ሰዎች የሚያውቁን፣ የሚሰማቸውን፣ እና የሚመስላቸውን ለማስተጋባት ሠዓሊዎች ቀለምን፣ ቅርፅን፣ ቅንብር (texture)፣ ክፈፍ/ቢጋር (form)፣ እና ስፍራ/ቦታ እንዴት እንደሚጠቀሙ መግለፅ።
- የኪነጥበብ ሥራዎችን በመመልከት ሠዓሊዎች ስለሰዎች፣ ሥፍራዎች/ቦታ፣ እና ድርጊቶች/ክስተቶችን እንዴት አድርገው እንደሚገልጹ ማስረዳት።
- የኪነጥበብ ሥራዎችን ለመፍጠር ሃሳብ እና የአካሄዱ ሥርአት እንዴት እንደሚመነጭ መለየት።

### ስነጥበብ ፈጠራ እና ግንኙነት/ማያያዝ

- ቀለም፣ መስመር፣ ቅርፅ፣ ቅንብር (texture)፣ ክፈፍ/ቢጋር (form)፣ እና ስፍራ/ቦታ በመጠቀም የሰዎችን አካላዊ ይዘት፣ እንስሳት፣ እና በአካባቢ ያሉ ግዑዝ ነገሮችን መግለጽ፣ማሳየት/ማመልከት።
- ቀለም፣ መስመር፣ ቅርፅ፣ ቅንብር (texture)፣ ክፈፍ/ቢጋር (form)፣ እና ስፍራ/ቦታ በመጠቀም አስተሳሰብ/ሃሳብ ከምልከታ/አስተውሎት፣ ትውስታ፣ ሃሳባዊ /ልብ ወለድ/ግምት (imagination) ማሳየት።
- የኪነጥበብ ባሕርይ የሚዳስስ ምስል መፍጠር፡- ቀለም፣ መስመር/ፈር፣ ቅርፅ፣ ቅንብር (texture)፣ ክፈፍ/ቢጋር (form)፣ እና የንድፍ መሠረተ ሐሳብ፡- ደብዛ/ቅጥ አምባር (pattern)፣ ድግግሞሽ፣ ንፅፅር/ልዩነት፣እና በማመዛዘን የግል ትርጉም መግለጽ።

## ሙዚቃ

### ሙዚቃ መጫወት

- የተለያዩ የተለጠጠ ድምፅ ቃናዎችን ለመዘመር በተስማሚ የድምፅ ቅላፄ ዘዴ መጠቀም።
- ልዩ ልዩ ዜማዎችን የድምፅ ቃና በቅላፄ-ሐረግ  ቅኝት ማዜም/መዘመር።
- ለመማሪያ ክፍል ውስጥ መሳሪያዎች ተገቢውን የመጫወቻ ዘዴ ማሳየት።
- ያገር ፍቅር ያለበት ዝማሬዎችን በመዘመር ዓላማቸውን መግለጽ።

### የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- ቀላል የስንኝ፣ እና የድምፅ ቃና/ጥርቀት፣ ሐረጎችን እና ምልክቶችን ማንበብ።

### የሙዚቃ ምላሽ/ዝንባሌ

- ከድምፅ አወጣጥ ዘዴ በመነሳት በክፍል ውስጥ የሚገኙ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ድምፆችን ምድብ መግለጽ።
- ሙዚቃ የማይጨምር-የማይቀንስ የድምፅ ምት/ድለቃ እየተዘመረ ወይም እየተሰማ በተለያየ ሚትርስ/meters መንቀሳቀስ።
- በቤት ውስጥ፣ በት/ቤት፣ እና በማህበረሰብ ስለ ሙዚቃ አጠቃቀም መግለጽ።

## የሰውነት ማጠንከሪያ ትምህርት

### የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች

- በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ፣ ግለሰቦች በተለያዩ ፍጥነቶች እንዴት በመማር ደረጃዎች ውስጥ እንደሚገሰግሱ/እንደሚሻሻሉ እውቅና መስጠት።
- የአንድ ሰው ችሎታ/እውቀት እድገት ውጤት ከባለፈው ልምድ፣ የተፈጥሮ ችሎታ፣ እና የልምምድ ውጤት የሚመነጭ መሆኑን መገንዘብ።
- ከጊዜ ወደጊዜ ከልምድ የተነሳ ጥበብ፣ ችሎታ፣ ሙያ፣ እንደሚዳብር መገንዘብ።
- አዎንታዊ/መልካም አስተያየት በክዋኔ/አፈጻጸም ላይ አስፈላጊነቱን መገንዘብ።
- ጊዜ/ፍጥነት፣ ኃይል፣ እና ፍሰት የመለየት ችሎታ ማሳየት።
- ማሳደድ/ማባረር፣ ሽሽት፣ እና ማምለጥ/ማፈትለክ ችሎታን ማሳየት።
- ከእቃ እና ወይም ከሰው ጋር እንቅስቃሴ የማድረግ ችሎታ ማሳየት።

### የግልና የማህበራዊ ሃላፊነት

- በአካል እንቅስቃሴ ቦታዎች ከሌሎች ጋር በብቃት ሥራ/ሪ።
- የማህበረሰባዊነት ስሜትን የሚፈጥር ግኑኝነቶች መገንባት እና ማጠንከር/መጠበቅ።

## የጤና ትምህርት

### የአእምሮ እና የስሜት ጤንነት

- ተስማሚ/ተገቢ የመገናኛ ዘይቤ ማወቅ።
- ለተለያዩ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ ስሜቶች እና ምላሾችን መመርመር/መፈተን።
- የግል ደህንነትን የሚያዳብሩ ነገሮችን ለይቶ ማወቅ።
- ውሳኔ ለመስጠት ያሉትን አማራጮች ለይቶ ማወቅ።
- ለኣንድ ሰው ልዩነት ኣስተዋፅኦ የሚያደርጉ አወንታዊና ኣሉታዊ የጠባይ ባህርያትን መለየት።
- በቤተሰብ ውስጥ የሚሆን ጫና/ውጥረት መንስኤዎችን ለይቶ ማወቅ።

### አልኮል፣ትምባሆ/ሲጋራ፣ እና ሌሎች መዳኒቶች (ATOD)

- የመድኃኒትን ትክክለኛ አጠቃቀም ለይቶ ማወቅ።
- ትምባሆ/ሲጋራ መጠቀም እንዴት ለጤንነት ጠንቅ/የሚጎዳ እንደሆነ ለይ።
- አልኮል መጠቀም በሰውነት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መለየት።
- ለመድኃኒት/እፅ ላለመጠቀም የሚያስችሉ መንገዶችን መለየት።

## አስተሳሰብና የአካዴሚያዊ ስኬት ክሂሎቶች

**የማሰብ እና የአካደሚ ስኬታማነት ክህሎት**ቅልጥፍና እና ትብብር በትምህርት አሰጣጥ ላይ የተካተቱ ናቸው።

**ቅልጥፍና**—ለአንድ ችግር ወይም ሃሳብ በርካታ ምላሾችን ማፍለቅ።

- በበርካታ ስልቶች በመጠቀም ሃሳቦችን ማፍለቅ።
- ጥያቄዎችን በተለያዩ መንገዶች መጠየቅ ።

**ትብብር**፡- የቡድኑን ግብ ለመድረስ በውጤታማነት እና በመከባበር መሥራት።

- በውጤታማነት ከሌሎች ጋር ኣብሮ በመስራት የቡድን ሰው የመሆን ዝንባሌ ማሳየት።
- የቡድን ግብ ለመምታት እርምጃዎችን ማጣራትና መለየት።
- የቡድን ግብ ለመድረስ ሃላፊነት የመጋራት ኣማራጮችን መለየትና መተንተን።